የረቡዕ ህዳር 14 1998 ዓም ( ኖቨምበር 23 2005)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

### <u>የቤተ ዘመዱ ይታያል ጉዱ</u>

የዓለም ታሪክ  መመዝገብ ከጀመረበት ዘመን አንስቶ፥ የዓለም ሕዝቦች በተለያዩ  ቅርፅና ይዘት በላቸው መንግሥታትና ሥርዓቶች ሲገዙም ሲተዳደሩም ቆይተዋል፡ ይህ ሂደትም እየቀጠለ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው፥ እስከ አሁኑ ክፍል ዘመን ድረስ።  በሀገር፥ በባህል፥ በቋንቋ፥ በሃይማኖት፥ በታሪክ ፥ በነገድ፥ በዘር፥ በብሔር፥ በጎሳና በመደብ ወዘተ እያለ በመውረድና ከዚያም ዝቅ ሲል በቤተሰብ ተጠናክሮና ተሳስሮ፥ መንግሥት ሲመሠረትና ሲፈርስ ቆየቷል። ከላይ የተዘረዘሩት የመንግሥታትና የሥርዓት ዓይነቶች ሊፈራርሱ  የበቁትም አንድ መሠረታዊ ባኅርይ ስሌላቸው ነው። ሁሉም ዴሞክራሲያዊ አልነበሩም። ሊሆኑም አይችሉም።  ሌላውን ለጊዜው እንለፈውና፤ በዘመናችን በዓለም ውስጥ ካሉት የተለያዩ የመንግሥታት ዓይነቶችና ይዘቶች፥ ቅርጾችና ሥርዓቶች ሁሉ፥ ለየት ባለ መልኩ ያሉትን ሁለት መንግሥቶች መጥቀስ እንፈልጋለን። እነርሱም፥ በሃይማኖት ሥርዓት የተመሠረተው የኢራኑን ቲዮክራሰ (ሥነ መለኮት) መንግሥትና ፥ በኢትዮጵያ ውስጥ፥ ከአንድ ብሔር አልፎ ተርፎ በቤተዘመድ ዙሪያ ተሰባስቦና  ተጠናክሮ ኢትዮጵያን የሚገዛው የአድዋ ቤተሰብ ቡድን ነው።  እነኝህን ሁለት የመንግሥት ዓይነቶች ለአብነት ለመጥቀስ የፈለግነው፥ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ለሚኖር ሕዝብ የማይስማሙ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፥ ለማመንም በሚያስቸግር ሁኔታ መንግሥት አዋቅረው እንዲቀጥሉ መደረጋቸውም ጭምር ነው።  የሌላውን ሀገር፥ ማለት የኢራኑን የመንግሥት አወቃቀርና ይዘት እንኳን ማንነትና አካሄድ መዘርዘሩን፥  በሌላ ሀገር የውስጥ ጉዳይ እንደ መግባት ስለምንቆጥረው፤ ብዙም አያገባንም። ይልቁንም፥ ወደ ሀገራችን ጉዳይ፥ ወደራሳችን ችግርና ሁኔታ  ማተኮሩን መርጠናል።

እንዲያው  ዝባዝኬ ሳናበዛ፥እንዲሁም ያለምንም አገም ጠቀም በቀጥታ ወደ ፍሬ ነገሩ መግባት አለብን ካልን፥ ሀገራችን በእርግዕጥ በምን ዓይነት ቡድን፥ ብሎም በቅርብ የተሳሰረ የቤተ ሰብ ኮሚቴ የምትገዛ መሆኗን ማጤን ይኖርብናል። ዛሬ ሀገራችን፥ እጅግ ሲዘነዘር፥ በጎጠኞች፥ ሲለጠጥ ደግሞ በብሄረተኞች የምትገዛ መስሎ ቢታይም፥ በዕርግጥ ማነኛውንም መንግሥታዊ ሥልጣን በመዳፋቸው አስገብተው ሀገሪቱን እንቀጥቅጠው የሚገዙ፥ የአንድ ቤተሰብ አባላት ብቻ ናቸው። ሌላው ሁሉ አገብጋቢና ጋሻ-ጃግሬ ነው። አገብጋቢዎችና ጋሻጃግሬዎች ደግሞ፥ እንኳንስ፥ ወደ ሥልጣን ሰገነት ሊቀርቡ ቀርቶ፥ የድግሱ ገፈት ተቋደሾች ለመሆን እንኳ ዕድል የሚያገኙ አልሆኑም። ፍርፋሪውን ግን ከማንም የበለጠ እንዲያግበሰብሱት ይፈቀድላቸዋል።

እረ ለመሆኑ በቤ.ተሰብ ዙሪያ ተዋቅረውና ተጠናከረው የሀገሪቱን ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን በመጨምደድ፥ የኢ.ትዮጵያን ሕዝብ በማስለቀስ ያሉት ግለሰቦች እነማን ናቸው?

እነኝህ ግለሰቦች ከአንድ ብሔረሰብ የወጡ ይሁኑ እንጅ፥ ያንን ብሔረሰብ ይወክላሉ፥ ያገለግላሉ ማለት ያስቸግራል:: ቢሆንም ቅድሚያ የሚሰጡት እንዳለ ሆኖ፥ ዋናው አወቃቀራቸው ግን በቤተሰብ ቀለበት ዙሪያ የሚሽከረከር ነው:: ይህ በኢትዮጵያ ታሪክና ባህል ውስጥ ምንም ዓይነት ይሉኝታና ሃፍረት የሌለው የቤተሰብ ጉችሌ(ቡድን) አዋቃሪዎቹ መለስ ዜናዊና መሰሪው ስብኃት ነጋ ሲሆኑ፥ ሁለቱም የህወሓት ፖሊት ቢሮ አባላት ናቸው:: የስብኃት ነጋ እህት፥ ቅዱሳን ነገ የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና የመቀሌ ከንቲባ ነች:: ባሏ አለቃ ፀጋይ በርሀ ደግሞ የህወሓት ፖሊት ቢሮ አባልና የትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት ነው:: ሌላዋ የስብኃት እህት አበራሽ ነጋም እንዲሁ፥ ከሁለት የእህቷ ልጆች ጋር፥ ለአዲስ አበባ ምክር ቤት ተወዳድራ ሳይሳካለት ቀርቷል:: ሁለቱም የአቶ ነጋ ልጆች፥ደግሞ እናታቸው ልክ እንደ መለስ ዜናዊ እናት ኤርትራዊ ናቸው:: የስብሃት ነጋ እህት ደግሞ፥ የኤርትራው መከላካያ ሚኒስትር የስብሓት ኤፍሬም ሚስት ነች:: አርካበ ዕቁባይም የዋዛ አይደለም:: እህቱን የዳረው፥ የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ለሆነው ለአዲስ ዓለም ባሌማ ነው:: እንደዚሁም የእራሱ የአርካበ እቁባይ ሚስትም ንግስቲ ገብረ ክርስቶስ፥ የብርሃነ ገብር ክርስቶስ እህት ነች:: ብርሃነ ገብረ ክርስቶስ ማለት የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና ቀደም ሲል በአሜሪካ የወያኔ አምባሳደር የነበረ ሲሆን፥ በአሁኑ ወቅት ደግሞ፥ በብራስልስ የመለስ አፈ-ቀላጤ ሆኖ ያገለግላል:: በዙ ጊዜ ስሙ የማይጠቀሰውና የህወሓት ፖሊት ቢሮ አባል የሆነው አባይ ወልዱ፥ ባለቤቱ ትሩፋት ኪዳነማሪያምም እንደዚሁ የህወሓት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል፥ የፍትህና የፀጥታ ቤሮ ኃላፊ ነች:: ሌላው የማዕከላዊ ኮሚቴ ባል የሆነው መጠን አብራሃም በበኩሉ፥የአባይ ወልዱ የቅርብ ዘመድ ነው:: የመለስ ዜናዊና የብሔራዊ ም/ቤት ፀሐፊ የሆነው ሙሉጌታ ዓልምሰገድ፥አያቶች ወንድማማቾች ናቸው::መለስ ዜናዊ የትም ሀገር በሚሃድበት ወቅት ሁሉ ይህ የስጋ ዘመዱ ተከትሎት አብሮ ይሄዳል:: የመለስን ልጅ ክርስትና ያነሳው፥ጄኔራል ብርሃነ ነጋሽ( ወዲ መድኅን) ሲሆን ይህ ሰው ደግሞ የሀገሪቱና የቤተ መንግሥቱ የፀጥታ ኃላፊ ነው:: ይህ ግለሰብ፥ የሰሞኑን የፖሊቲካ እስረኞች ፥ ቤተ መንግሥት ተቀምጦ በዚህ አስገቡ፥ በዚያ አስወጡ እያለ የሚያዝዝ እንደሆነ ተደርሶበታል::

እንዲህ እየተባለ፥ ሁኔታውን በተዋረድ እስከ መጨረሻው መዘርዘር ይቻላል:: በአጠቃላይ ግን፥ ኢትዮጵያ የምትገዛው በአንድ ጎሳ ብቻ ሳይሆን በአንድ ቤተስብ አባላትም ጭምር ነው:: ይህ ብቻም ሳይሆን፥ የሀገሪቱ ቁልፍ ጉዳዮች በሙሉ የሚወሰኑት በእነኝህ ቤተሰብ አባላት ነው:: መለስ ዜናዊ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥመውና አደገኛ ሁኔታ ተፈጠረ ብሎ በሚርበተበት ጊዜ፥ ለምክር የሚቀመጠው፥ ከሚከተሉት የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ( ህወሓት) ሰዎች ጋር ብቻ ነው:: መለስ ስብሰባውን ሲከፍት በተደጋጋሚ የሚያስጠነቅቀው ነገር ቢኖር፥ አይትመኖ እዚኦም ርጎማት ( እነኝህን

እርጉሞች አትመኗቸው) የሚለውን መርዝ ነው:: እርጉሞች ብሎ የሚሰድባቸው ደግሞ የየትኛው ብሔር አባለት እንደሆኑ ሁሉም ያውቀዋል:: ለአስቸኳይ ስብሰባ የሚቀመጡት የህወሓት አባለት የሚከተሉት ናቸው::

1) መለስ ዜናዊ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ
2) ሙለጌታ ዓለም ሰገድ በጠቅላይ ምኒስቲሩ ቢሮ የፀጥታ ጽ/ ቤት ኃላፊ
3) ጌታቸው አሰፋ የደኅንነት ኃላፊ
4) በረከት ስምዖን
5) ጄኔራል ሳሞራ የኑስ የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም
6) ኢሳያስ ወ/ ጊዮርጊስ የደኅነነት ምክትል ሹም
7) ብርሃኔ ነጋሽ ( ወዲ መድኅን) የቤተ መንግሥት የፀጥታ ሽም ናቸው:: ስብኃት ነገም ሲያስፕውና ከመጠጡ የሚተርፈው ጊዜ ካለው÷ በዚህ ስብሰባ ላይ ይገኛል::

በዚህ ስብሰባ የተወሰነውን ውሳኔ በተግባር ለማስተርጎም ከዚህ የሥልጣን አካል ቀጥሎ÷ ሌላ የሥልጣን እርከን አለ:: ይህም የፖሊት ቤሮ የሚባለው ነው:: ይህ ስብሰባ÷ ፖሊቲካ የሚወራበት÷ የሀገሪቱ አጠቃላይ ሁኔታ የሚቃኝበት÷ ውይይት የሚሰጥበት÷ ግምገማ የሚካሄድበትና ድርጅታዊ ሥራ የሚሰራበት ነው:: በዚህም የፖሊቲ ቢሮ ስብሰባ የሚካፈሉት፤

1) መለስ ዜናዊ
2) ስዩም መስፍን
3) አርካበ ዕቀባይ
4) አባይ ፀሐይ
5) አባዲ ዘሞ
6) አባይ ወልዱ
7) አለቃ ፀጋየ በርሀ
8) ስብሀት ነጋና
9) ቴዎድሮስ ሐጎስ ናቸው::

ሀገሪቱ በዕርግጥ የምትገዛው በእነኝህ የቤተስብ አባላት÷ ወረድ ሲል ደግሞ÷ እራሳቸውን የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ግንባር ብለው በተደራጁ ግለሰቦች ነው:: ኤሕአዴግ በሚል ዳስ ስር የተሰባሰቡት ሌሎች የመለስ ዜናዊ አንጋቾችና ተስፎኞች ግን÷ ኢትዮጵያዊ ብኩርናቸውን÷ ስብዓዊ ክብራቸውንም ሆነ ሰብዕናቸውን ለጊዚያዊ ጥቅም የለወጡ ጉደኞች ናቸው:: ይህንን ደግሞ÷ ዘር ሳይለይ ለጥቅሙ የሰገደ ሁሉ÷ አማራ÷ኦሮሞ÷ ትግሬ÷ ጉራጌ÷ አደሬ÷ ወላይታ÷ ሀድያ÷ሲዳማ ÷ ሱማሌ ሳይል ሁሉም እያገኘው ነው:: መለስ ዜናዊ ሥልጣኑን አጋርቷል የሚለው የመከራከሪያ ቧልት÷ የተትረፈረፈውን ምግብ ለውሻ እንደመውርወር ካልሆነ በቀር÷አስተዋዩንና ታዛቢዉን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊያታልል አይችልም:: የቤተ ዘመድ መንግሥት ጉድ ደግሞ ይኸው እየታየ ነው:: የአስራ አራት ዓመታት የጎሳ ፖለቲካና ዘረኛ ሥርዓት ሀገሪቱን

ወደ ጥፋት ጎዳና ከሚያመራት በስተቀር ካለፉት ሥርዓቶች የተሻለ ሁኔታን ሊያመጣ አልቻለም። በኢትዮጵያ የነበሩት የአለፉት ሁለት ሥርዓቶች ፥ አያሌ ከባድና ቀላል ስህተቶች የፈፀሙ መሆናቸው ባያከራክርም፥ ዘረኞች ስለአልነበሩ፥ ሀገራቸውን በብሔር፥ በክልል፥ በሃይማኖትም ሆነ በቤተ ሰብ አለከፋፈሉም። ዜጎች በብሔራቸው መሠረት መገንጠል አለባቸው የሚል አንቀጽ በህገ መንግሥት አልቀረጹም። የኢትዮጵያን ሥርዓተ-ትምህርት፥ በክልልና በቋንቋ አላደራጁም። ኤርትራውያንን ከወድሞቻቸውና ከእህቶቻቸው ከኢትዮጵያውያን ጋር ተለያይተው እንዲኖሩ አላደረጉም። ይህን እያደረገ ያለው የመለስ ዜናዊ የቤተዘመድ ኮሚቴ አስተዳደር ነው።

ይህ ሥርዓት በግድ መለወጥ እንዳለበት የሚያከራክር ባይሆንም፥ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ አለብን በሚለው ግን እስካሁን ድረስ የጋራና የተባባረ ድምፅና ኃይል አልተገኘም። ይህ በጋራ ብሔራዊ ራዕይ ላይ የተመሠረተ የተባበረ ድምፅና ጠንካራ ኃይል መምጣቱ ግን የማይቀር ነው። ያንን ለማግኘት የተቃወሚ ድርጅቶች በሙሉ በከፍተኛ ዝግጅት ላይ መገኘት እንደሚገባቸው፥ የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያስገድዳቸቸው መሆኑን ሊያውቁት ይገባል።